# ከህወሓት/ኢህአዴግ ባሻገር

## ---ኢፍትሃዊ ቡድን ፍትሃዊ ሊሆን አይችልም--

## አክሎግ ቢራራ (ዶር)

## “We must learn to live together as brothers or perish together as fools.”

## Dr. Martin Luther King,

### ክፍል አንድ---ዐውደ ንባብ (Context)

*ይህ ተከታታይ ጽሁፍ ለምን አስፈለገ?*

*የኢትዮጵያ ሕዝብ አፋኙን፤ ጨካኙንና “በእድገት” ስም ድርጅታዊ መዝባሪውን የህወሓትንና ተባባሪዎቹን ስርዓት ለመለወጥ እንደሚችል አምናለሁ። መሰረታዊ ተከታታይ ችግሮች ግን በቀላሉ ሊፈቱ አይችሉም። መመካከር ያለብን አቢይ ጉዳይ፤ ይህ አምባገነናዊ ስርዓት ከተለወጠ በኋላ ኢትዮጵያ ምን አይነት ብሄራዊና ሁሉን አሳታፊ ራእይ፤ ተልእኮና የእድገት ሞዴል ያስፈልጋታል የሚለው ነው።*

*በዚህ **<u>በአምስት ክፍሎች</u>** በተከታታይ በማቀርበው ትንተናና የወደፊት ብሄራዊ የፖሊሲ አቅጣጫ፤*

1. *መጀመሪያ በአሁኑ ወቅት፤ የአገራችን የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ፤ ማህበረሰባዊ፤ ኢኮኖሚያዊ፤ ዲፕሎማሲያዊና ተመሳሳይ ገጽታዎች ምን ይመስላሉ? የሚለውን አቀርባለሁ።*

2. *በህወሓትና በአጋሮቹ ላይ ምን አይነት የሕዝብ ጥላቻ አለ፤ ጥላቻው ካለ እንዴት ሊፈታ ይችላል? የሚለውን አርእስት እገመግማለሁ። ጥላቻን በጥላቻ እንለውጣለን ማለት “ከድጡ ወደማጡ” ይሆናል። የጥላቻ ፖለቲካ መወገድ አለበት። ይህን በሚመለከት የመሰሉኝን መፍትሄዎች ሕዝብ፤ በተለይ ወጣቱ ትውልድ እንዲወያይባቸው እሰነዝራለሁ።*

3. *ኢትዮጵያ “የብሄር፤ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች (ከአሁን በኋላ ዘውግ ብየ የምጠራቸው) እስር ቤት ናት” የሚለውን ተቀብየ ስለማላውቅ፤ የእነዚህን ዘውጎች ጌጥነትና ለአንድ አገር ምሰረታ ወሳኝነት ተቀብለን፤ በተለይ ድምጻቸውና ተሳትፏቸው ገና እውቅና ላለገኙት ክፍሎች ምን አይነት መፍትሄ ይፈልጉ ይሆን? የሚለውን ጥያቄ አቀርባለሁ። ከሌሎች አገሮች ልምዶች የተማርኳቸውን ገንቢ ጽንሰ-ሃሳቦች ለታዳሚዎች እንወያይበት በሚል መንፈስ አቀርባለሁ።*

4. *በእኔ እምነት፤ የምንጋራው የአገር ትርጉም እየተሸረሸረ ነው። ኢትዮጵያዊነት የሚለውን እንደ ተራ ነገር እንወረውረዋለን እንጂ የጋራ እሴት ለማድረግ ብዙ ስራዎችን መስራት ግዴታችን ነው። አብሮነት ለጋራ አገር፤ ድህነትንና ኋላ ቀርነትን ለመቅረፍና ለጋራ ዜግነት ወሳኝ ጽንሰ-ሃሳቦች ስለሆኑ የወደፊቱን በሚመለከት ተመክሮዎቸን በአጭሩ ለውይይት እንዲሆኑ ለወጣቱ ትውልድ አቀርባለሁ።*

5. *ማንኛውም አገር በተለያዩ መንገዶች የእድገትን አቅጣጫዎች የሚያሳይና የሚመራ መንግሥት አለው። በኢትዮጵያ “የእድገታዊው መንግሥት” ያስገኛቸው የእድገት ውጤቶች እንዳሉ ሆኖ፤ የወደፊቱ በአብሮነት የተመሰረተ የኢትዮጵያ የልማት ሞዴል ምን መሆን አለበት በሚለው ዙሪያ ተመክሮዎቸን አቀርባለሁ።*

***መንደርደሪያ***

ኢትዮጵያ የጥቁር አፍሪካ አካል ናት። የጥቁር አፍሪካ ሕዝብ በልዩ ልዩ ቅኝ ገዢዎች ሲሰቃይ ከቆየ በኋላ “ነጻነቱን” መጎናጸፉ ለሁላችንም የሚያኮራ ነው። ሆኖም፤ የዚህ “ነጻነት” ዋናው ትርጉም በመሬት ላይ የሚታይና የሚዳሰስ ፍትህ፤ የሕግ የበላይነት፤ ዲሞክራሳዊ ስርዓት፤ ማህበረሰባዊ ጥቅምና የኃብት ባለቤትነት ሲኖረው ነው። በአብዛኛው፤ የጥቁር አፍሪካ አገሮች ግዙፍ የተፈጥሮ ኃብት ቢኖራቸውም የዚህ ኃብት ተጠቃሚዎች እነሱ አይደሉም። አሁንም የውጭ ኃይሎች፤ ኢንቨስተሮችና የተወሰኑ የአገር ውስጥ ልሂቃን ናቸው። የኢትዮጵያን ሁኔታ ስገመግማቸው፤ የግራ ክንፉ ዱሮ “አቀባባይ ከበርቴ” ብሎ የሚጠራው ክስተት በረቀቀ ሁኔታ ስር እየሰደደ ነው። የገቢና የኑሮ ልዩነቶች ጥልቀትና ስፋት ይዘዋል። ይህ አዲስ የመደብ ክስተት፤ ግጭቶችንና አለመረጋጋትን ፈጥሯል። ዛየር ምሳሌ ናት።

እንደ ቦትስዋና፤ ጋና፤ ደቡብ አፍሪካ ከመሳሰሉት ዲሞክራሳዊ አገሮች ውጭ፤ የአፍሪካ አገሮች “ነጻነታቸውን” ተጎናጽፈዋል ቢባልም፤ በራሳቸው የፖለቲካ ልሂቃን እየታፈኑ፤ እየተጨፈጨፉ፤ ድርጅታዊ ምዝበራዎች እየተካሄዱባቸውና ወጣቱ ትውልዳቸው

እየተሰደደባቸው ይገኛሉ። ነጻነቷን አስከብራ የቆየችው፤ በጥንታዊ ስልጣኔዋ የታወቀችውና ለመላው የጥቁር ሕዝብ ተምሳሌት የነበረችው **አገራችን ኢትዮጵያ በራሷ "ልጆች" ደምታለች።** የራሷ ልጆች ከድተዋታል፤ አሳንሰዋታል፤ ጥገኛ አድርገዋታል። በነጻነቱና "በአትንኩኝ" ባይነቱ የሚታወቀው፤ እንደ **"ዢንጉርጉሩ"** ነብር የሚያምረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የአብሮነትን፤ የመደጋገፍን፤ የወንድማማችነትን/የእህትማማችነትን፤ የፍቅርንና የማህበረሰባዊ ትሥስርን እሴቶች ተቀብሎ ጠንካራና ራሱን የቻለ ሕብረተሰብ እንዳይፈጥር ታፍኖ ቆይቷል። ራሱን ከዘመናዊ ባርነት ነጻ ለማውጣት ከፈለገ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ **ዲሞክራሳዊ ስርዓትንና ለዚህ ወሳኝ የሆነውን አብሮነትን** ማጠናከር ግዴታው ነው።

**በብሄር ነጻ አውጭነት ስም፤** ለጥቂቶች የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት እንዲያገለግል ታስቦ በሕዝብ ላይ የተጫነው የህወሓት/ኢህአዴግ የፖለቲካና የእድገት አመራር ዶር ማርቲን ሉዘር ኪንግ እንደለገጹትና እንዳሳሰቡት ዘለዓለማዊ ተመክሮ፤ "በወንድማማችነት አብረን ለመኖር ከፈለግን፤ መማር አለብን፤ አለያ ልክ እንደ ደንቆሮዎች/ጅሎች አብረን እንጠፋለን" የሚለውን ያንጸባርቃል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሞኝና ተላላ፤ ደንቆረና ጅል ሆኖ አያውቅም። ይህ ባህል እንዳለ ሆኖ፤ ባለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት ራሱን ለጅቦች አጋልጧል። ድህነት ስር እየሰደደ ነው። ሕዝቡ፤ ኃብቱንና ክብሩን ተነጥቋል። በህወሓት የበላይነት የሚመራው ስርዓት ይኼን የሚዘገንን የገቢና የኑሮ ልዩነት የፈጠረው "ለጭቁን ብሄሮች" ቁሜአለሁ በሚል **የህወሓት ማዘንጊያ ስልት** ነው።

የኢትዮጵያ ዘውጎች ነጻነትና ሰብአዊ መብቶች መከበር፤ የራሳቸውን የውስጥ አስተዳደር በበላይነት መምራትና በራሳቸው የተፈጥሮ ኃብት ተጠቃሚ መሆን **ለኢትዮጲያዊነትና ለኢትዮጵያ ሉዐላዊነት ወሳኝ** ነው። በየዓመቱ ባህላቸውን ማክበር በቂ አይደለም፤ ይኼንማ ደርግም አድርጎታል። ዋናው መስፈርት አቅማቸውን ማጠናከር፤ የፖለቲካ ኢኮኖሚ መብታቸው አመራር ወሳኞች፤ በተለይ የተፈጥሮ ኃብታቸው ባለቤትና ተጠቃሚዎች ከማድረጉ ላይ ነው። የኦሞ ሸለቆና የሌሎች ዘውጎች መብቶች በሸንገላ ሊታለፉና ሊስተናገዱ አይችሉም።

ለዚህ "**በብሄር ነጻነት ስም"** ለሚነገድበት የተሳሳተ ጽንሰ-ሃሳብ ግብአት ከሰጡት ከውጭ መንግሥታትና "ባለሞያዎች" በተጨማሪ፤ በኢትዮጵያ ምሁራንና ልሂቃን መካከል  ሁኔታዎችን የሚያባብስ ትንተናና ምክር ሲለገስ ቆይቷል። ዛሬ በፌስቡክና በሌሎች ዘመናዊ መገናኛዎች አማካይነት የኢትዮጵያን ወንድማማች/እህትማማች ሕዝብ የሚለያዩ ትችቶች ይካሄዳሉ። በማንነት ስም፤ ብዙው ለጎጀውና ለጥቅሙ ብቻ ይታገላል። ህወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘበት ጀምሮ ያለው ታሪክ ያስተማረኝ ሃቅ አንድ ነው። ይኼውም፤ ማንኛውም ዜጋ የህወሓትን/የኢህአዴግን **አምባገነናዊ አገዛዝ አወንታዊ** ፕሮፓጋንዳ ሲያስተጋባና ወጣቱን ትውልድ ሲያስተምር የቆየው፤ "በወንድማማችነት አብሮ መኖርንና" በአብሮነት መሰረታዊ ችግሮችን መፍታትን አይደለም። ለህወሓትና ለድርጅቱ ታማኝና አገልጋይ የሆኑ ግለሰቦችና ስብስቦች ለጋራ አገር፤ ለጋርዮሽ ልማት፤ ለአብሮነትና ለፍትሃዊ እድገት ደንታ የላቸውም።

ህወሓቶችና ታማኞቻቸው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በመላው የኢትዮጵያ ዘውጎች እንዳይደገፍ ሲያደርጉ መቆየታቸው የአደባባይ ምስጢር ነው። ኢትዮጵያዊነትን እንደ ተራ ሸቀጥ ሲፈልጉ የሚቸር፤ ሳይፈልጉ የሚነጠቅ አድርገውት ቆይተዋል። ልክ እንደ መሬት ነጠቃው ማለት ነው። አቶ ለማ መገርሳ እንደተናገረው **"ኢትዮጵያዊነት መንፈስ ነው"** የሚለውን ጽንሰ-ሃሳብ ለምንቀበል ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ማንም ባለሥልጣን፤ ማንም የፖለቲካ ፓርቲ፤ ማንም የመንግሥት መሪ ይኼን የኢትዮጵያዊነት መንፈስ ሊነጥቀን መፍቀድ የለብንም።

የ'አብዮታዊ ዲሞክራሲና' ከዚህ ጋር የተያያዘው 'የእድገታዊ መንግሥት' **ርእዮትና ተልእኮ፤** ለጥቂቶች ልሂቃንና ለደጋፊዎቻቸው አገልግሎትና ጥቅም የተመሰረቱና ሕገ መንግሥታዊና ተቋማዊ የሆኑ ክስተቶች ናቸው። Revoutionary Democracy (አብዮታዊ ዲሞክራሲ) የአምባገነኖች መሳሪያ ነው። "የብሄር፤ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች እኩለነት" የሚለው መርህ፤ በዘውግ ማር ይቀባ እንጂ፤ **የህወሓት የፖለቲካ ጥላቻ መሰረትና ምክንያት ሆኖ የሚያገለግል የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት** ነው። "አብዮታዊ ዲሞክራሲና እድገታዊ መንግሥት" ተብየዎቹ፤ "በወንድማማችነት አብሮ ለመኖር" የሚያስችል ትምህርትን ለማስተማር የተጻነሱ አይደሉም። ያስተማሩትና ያስተጋቡት ልዩነቶችን ነው። ያባባሱት የገቢና የኃብት ኢፍትሃዊነትን ነው። የህወሓት/ኢህአዴግ ሕገ መንግሥት ተግባሩ የህወሓትንና የታማኞቹን ጥቅም ማገልገል ነው። ይህ እስከሆነ ድረስ **"አብዮታዊም፤ ዲሞክራሳዊም"** ሊሆን አይችልም።

"ዲሞክራሲ" የሚለውን መርህ "አብዮታዊ" ከሚለው ጋር ያጣመሩበት ዋና ምክንያት፤ ለጥቂቶች፤ በጥቂቶች የሚለውን ለማጠናከርና ሕጋዊ ለማድረግ ነው። **የዲሞክራሲን ትርጉም የሚወስነው ህወሓትና አገልጋይ ድርጅቶቹ ናቸው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ** አይደለም። ለዚህ ነው ምርጫዎች የሚጭበረበሩት፤ የዜጎችን መብቶች እንደ ተራ ነገር የሚነጠቁት፤ የፖለቲካ እስረኞችን ዛሬ ፈተው ነገ የሚያስሩበት፤ በልማት ስም መሬቶች ተወርሰው ለታማኞች የሚሰጥት። ሁሉም አፈናና ምዝበራ የሚደረገው በሕዝብ ስም ነው።

ህወሓቶችና ታማኞቻቸው የሚፈልጉትና አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገው የተለያዩ ናቸው። ተራው ኢትዮጵያዊ ብቻ ሳይሆን፤ የኢትዮጵያ ዘውጎች አባላት የሚመኙትና የሚፈልጉት አብሮና ተባብሮ መሰረታዊ ችግሮችን መቅረፍ ነው። ለምሳሌ፤ ረሃብን፤ ስራ አጥነትን፤ ድህነትንን። ህወሓትም ቢወገድ፤ ችግሮችን ለመቅረፍ፤ ሳይሰለቹና በተከታታይ፤ አብሮነትን፤ ማህበረሰባዊ ትሥስርን፤ ፍቅርን ማጠናከርን ይጠይቃል። ሕዝብን ከሕዝብ መከፋፈልና የዘውግ ጥላቻን ማዛመት የዚህ ተጻራሪ ናቸው። ዶር ማርቲን ሉዘር ኪንግ እንዳሳሰቡት ይህ ዘውጎችንም የሚመለከት ሁኔታ፤ በነጭና በጥቁር መካከል በአሜሪካ ለመቶዎች አመታት የቆየው ጥላቻ የሚዘገንን የኑሮ ልዩነቶችን ፈጥሯል። የገቢና የኑሮ ልዩነት ብዙ መንስኤዎች አሉት። ከስግብግብነትና ከሙሰኛነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው የኢኮኖሚ የኑሮና የገቢ ልዩነት ክስተት፤ ቀስ በቀስ፤ ከአሜሪካና ከሌሎች አገሮች ወደ አገራችን እየተዛመተ ነው። ይህን ክስተት ከጅምሩ

ካልታገልነው ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚያመዝን አምናለሁ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሙስናን ከቁንጮው ለማስወገድ መቻል አለበት። እየደማ ሊኖር አይችል።

በየትኛውም ዓለም በገቢና በኑሮ ልዩነቶች ላይ የሚታየው አሉታዊ መረጃ ተመሳሳይ ነው። አገርን ያጠፋል። የከፋፍለህ ግዛውና ብላው ስልት 'ለወንድማማቾች/እህትማማቾ' አብሮ መጥፋት መሰረት ነው። ለአዲስ ሃብታሞችም ቢሆን አብሮ መጥፋትን ያስከትላል። የተፈጥሮ ኃብት ባለጸጋ የሆነችው ቬኔዙየላ ምሳሌ ናት።

ህወሓቶች ሌላውን አጥፍቶ አብሮ መጥፋት ድንቁርና መሆኑን ፈጽሞ አይቀበሉም። አብሮ መስራት ብልህነት መሆኑን አያስተናግዱም። አብሮነትን የሚያስተጋባ የመንግሥት ስርዓት የአገርን ዘላቂነትና ሉዐላዊነት፤ የሕዝብን አንድነት መሰረት አድርጎ ዋናዎቹን መዋቅራዊ የሆኑ የሕዝብ ጠላቶችን ለመቅረፍ የሚያስችል ሁኔታዎችን ይፈጥራል። እነዚህ ችግሮች በጋራ እንጅ በግለሰብ፤ በአንድ መሪ፤ በአንድ ቡድን፤ በአንድ ዘውግ ትግል አይፈቱም። በህወሓት/ኢህአዴግ ብቻ የበላይነት አይፈቱም።

**የብሄራዊ ራእይ ወሳኝነት**

የኢትዮጵያን መሰረታውዊ ችግሮች በዘላቂነትና በሚያስተማምን ደረጃ ለመቅረፍ የምንችለው፤ ፍትሃዊ፤ ሁሉን አሳታፊና ተሳታፊ አድርጎ፤ ሁሉንም ዘውጎች በእኩልነት የሚያስተናግድ፤ **በሕግ የበላይነት የተመሰረተ ዲሞክራሳዊ ስርዓት** ለመመስረት ቆርጦ በመነሳትና ተባብሮ በመስራት ነው። ይህ የሁላችንም ታሪካዊ ግዴታ ነው።

የወደፊቱን የሕዝቡን የኑሮ ሁኔታዎች ለማሻሻል **መንፈሳዊ "ተሃድሶ" ወሳኝ** ነው። "ለኔ" ከሚለው ስግብግብነት "ለእኛ" ወደሚለው መሸጋገር። "በለው" ከሚለው አጥፊነት፤ "እናዳምጠው" ወድሚለው መሸጋገር ወዘተ። መንፈሳዊ ተሃድሶ፤ ሕዝባዊና ፍትሃዊ ራእይ ከሌለ የኢኮኖሚ "ተነሃድሶ" አይቻልም።

ህወሓት/ኢህአዴግ አዘናጊ የሆኑ ለውጦችን (Cosmetic changes) ከማስተናገድ ውጭ፤ ከሕዝቡ ፍላጎትና ምኞት ጋር የሚመጣጠን መሰረታዊ ለውጥ ለማካሄድ አይፈልግም። መሰረታዊ ለውጥ ለመተግበር ራሱን ሙሉ በሙሉ መለወጥና ሕዝብን የስልጣኑ ባለቤት የሚያደርግ ተተኪ ስርዓት እንዲመሰረት መፍቀድ አለበት።

"ግምገማ" አድርጎ፤ የአመራር ድክመቶቹን ይፋ ካደረገና ሕዝቡን "ይቅርታ" ከጠየቀ በኋላ ህወሓት/ኢህአዴግ አሁንም ለኢትዮጵያ "ተሃድሶ (Renaissance) አስተማማኝ ብቸኛ ድርጅት እኔ ብቻ ነኝ ብሏል። ባወጣው መግለጫ ለማሳመን እንደሞከረው፤ አባል ድርጅቶች፤ ዘውጎች፤ የግል ባለኃብቶች፤ ሴቶች፤ ወጣቶች፤ በህወሓት የበላይነት የሚመራው "የመከላከያና የደህንነት" ተቋማትና አባላት፤ ምሁራን፤ ተቀናቃኝ ፓርቲዎችና ሌሎች የሕብረተሰብ አባላት በሙሉ ለገዢው ፓርቲ ቀጣይነት ታማኝ እንዲሆኑ ጥሪ አድርጓል። **ድክመቶቹ የአመራር ድክመት እንጅ የድርጅት ራእይ፤ ተልእኮ፤ ፕሮግራምና የባጀት አመዳደብ ክፍተቶች እንዳልሆኑ ጠቁሟል። ያሰመረበት፤ ኢትዮጵያ ጥገናዊ እንጅ፤ መሰረታዊ ለውጥ እንደማያስፈልጋት ነው።**

በተለይ የሚያስደነግጠው የተሳሳተ አቀራረብ ለወጣቱ ትውልድ የተደረገው የመሸንገያ ጥሪ ነው። ይህ ትውልድ ቢያንስ ለአለፉት አምስት ዓመታት ራሱን ለህወሓት/ኢህአዴግ አልሞ ተኳሾች አጋልጦ መስዋእት እንደሆነ ረስቶታል። ወጣቱን ትውልድ እየጨፈጨፈ፤ ለስደት እያጋለጠ፤ **የፈታቸውን መልሶ እያሰረ፤** ዜጎችን እያስፈራራ ወጣቱን ትውልድ "አለሁልህ" ይለዋል። ይህ የማዘናጊያ ዘዴ ነው። ኢፍትሃዊ የሆነ ቡድን በሕግ የበላይነት አያምንም የምለው ለዚህ ነው። አል-ጃዚራ በApril 1, 2018 ባወጣው መረጃ መሰረት ስመለከተው፤ በሁለት ዓመታት ውስጥ የደነገገው ሁለተኛው አስቸኳይ **"አንድ ሽህ አንድ መቶ** " ወገኖቻችን እንዲታሰሩ አድርጓል።

**አነጋጋሪው የዶር አብይ "ሹመት"**

ኢትዮጵያ ባለፈ ታሪክ ያልተበከሉ፤ ማንነታቸውንና ኢትዮጵያዊነታቸውን ከልብ የተቀበሉ፤ ችሎታና አስተዋይነት ያላቸው መሪዎች ያስፈልጓታል። የአገር መሪ ሲባል እኔ የሚገባኝ ኢትዮጵያዊ መሪ የሚለው ነው። ዘውግ፤ አካባቢና ኃይማኖት በሁለተኛ ደረጃ የሚታዩ ናቸው።

እኔ ዶር አብይን የማየው በአስተሳሰቡ ጥራትና በኢትዮጵያዊነቱ ነው። የሚወክለው የአመራር ጽንሰ-ሃሳብ ሁሉንም ኢትዮጵያዊያን ለማስተናገድ እምቅ ችሎታ እንዳለው እገምታለሁ።

ይሕ እምቅ ችሎታ በተናጠል ሊሰራ አይችልም። ለመሰረታዊ ለውጥ የቆሙ፤ ከአድልዎ፤ ከፖለቲካ ሥልጣን ጋር የተያየዘውን **"የሙስናና የኪራይ ሰብሳቢነት" ባህል ለማጽዳት የወሰኑ፤** ለሕዝብ አገልግሎት፤ ለነጻነትና ለመብቶች መከበር ቆርጠው የተነሱ፤ በፍትህ ስኬታማነት የሚያምኑ፤ የማንም ፓርቲ ተቀጥላ ያልሆኑ ወዘተ ግለሰቦች ከአዲሱ መሪ ጋር ተባባሪ እንዲሆኑ ማድረግን ይጠይቃል። የፈለገውን ያህል ችሎታ ቢኖረው አንድ መሪ በራሱ የሚወስናቸውና የሚተገብራቸው ፕሮግራሞች የሉም። አመራር የጋራ ነው።

ይኼም ሆኖ የአሁኑ አምባበነናዊ ስርዓት በቀላሉ ይፈታል ብሎ ማመን ሞኝነት ነው።

ዛሬ አነጋጋሪ የሆነው፤ የዶር አብይ አህመድ የኢህአዴግ ሊቀመንበር ሆኖ መመረጥ ተስፋ የሚሰጥ ጭላንጭል ሆኗል። ተመልካቾች የተለያዩ ትርጎሞች ሰጥተውታል። ለአንዳንድ ተመልካቾች የአብይ መመረጥ "ምንም አይነት ለውጥ" ሊያመጣ አያስችልም ወደሚል

ድምዳሜ ገፍቷቸዋል። እኔም ከምርጫው በፊት ባቀርብኳቸው ትንተናዎች አዲስ ጠቅላይ ሚንስተር መመረጡ በተናጠል የኢትዮጵያን ሕዝብ መሰረታዊ ችግሮች ሊፈታ እንደማይችል አስምሬበታለሁ። ይህ እንዳለ ሆኖ አብይ ጥቃቅን ለውጦችን ሊያመጣ አይችልም ለማለት አይቻልም። ጥቃቅን ለውጦች ሲደማመሩ ለመሰረታዊ ለውጥ ይረዳሉ። ለምሳሌ፤

1. የፖለቲካ እስረኞችን በሙሉ ሳይውል ሳያድር ለማስፈታት ይችል ይሆናል።
2. ከቀያቸው የተወገዱትን ኦሮሞዎች፤ አማራዎችና ሌሎችን ወደ ቀያቸው ለመመለስ ይችላል።
3. የሙስሊሞችን የሙብት ጥያቄ መልስ ሊሰጠው ይችላል።
4. ለወጣቱ ትውልድ የትእግስት ጊዜ የሚሸምት የስራ እድል ፕሮግራም ሊፈጥር ይችላል።
5. ዛሬ **<u>ለአገራችንና ለ110 ሚሊየን</u>** ሕዝብ ቀውስ መንስኤ የሆነውን አፋኙንና ጨካኙን የፓራቲና የመንግሥት ግፍ (State sponsored violence) ልያስቆመው ይችላል። ይኼን ካደረገ **<u>ከሕዝቡ ተአመኔታንና ድጋፍን ሊያገኝ</u>** የሚችልበትን ሁኔታ ይፈጥራል። ሕዝቡ ከደገፈው ብዙ ለውጦችን ስኬታማ የማድረግ እድል አለው። ይህ ምኞት ሊሆን ይችላል። ላሰምርበት የምፈልገው ጽንሰ-ሃሳብ፤ ዶር አብይ በህይወት የሌለውን የመለስ ዜናዊንን ራእይ፤ ተልእኮና "እድገታዊ መንግሥት" መርህ ይዞ ተመጣጣኝ ለውጦችን ስኬታማ ለማድረግ አይችልም።
6. ሌላው ሊያደርገው የሚችለው የሁሉንም ዘውጎች፤ በተለይ የተረሲትን አቅም ለማጠናከር ይችላል፤ የእነሱን ግብዓት በመጠየቅ።

ስለዚህ፤ ጥገናዊ ለውጥ ዋጋና ጥቅም አለው። ስርዓት ወለድ የሆኑትን መሰረታዊ ችግሮችን ግን ሊፈታ እንደማይችል ለማሳውብ እፈልጋለሁ። **<u>ግን፤ ጥገናዊ ለውጥ ለመሰረታዊ ለውጦች በር ካልከፈተ፤ የሕዝቡ ጥያቄ ሙሉ በሙሉ መልስ አያገኝም። በመሆኑም፤ የሕዝቡ ትግል ይቀጥላል።</u>**

ይህ ወጣት መሪ ማነው? ዶር አብይ፤ በወጣትነቱ የኢህአዴግ አባል ሆኖ ያደገ፤ በህወሓት/ኢህአዴግ ርእዮት የታነጸ፤ በመሰረተ ተልእኮውና ስራው ያመነ ነው ቢባል ትክክል ነው። ከዚህ ባሻገር መታየት ያለበት ግን፤ አብይ የራሱ የሆኑ መለያዎች አሉት።

- ለሰብአዊ ሙብቶች መከበር፤ ለወጣቱ ትውልድ ህይወትና ኑሮ መሻሻል፤ ለኣብሮነት መጠናከር፤ ለኢትዮጵያ ሉዐላዊነት፤ ዘላቂነትና ለብሄራዊ ጠንካራነት አስተዋጾዎች አላደረገም ለማለት ግን አይቻልም። የመንፈሳዊ ንቃትና ብቃት ያሳያል። ግለሰባዊ ሃቀኛነት ያሳያል። በሰብእነቱ፤ በኃማኖቱና በዘውጉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ስርጭት ያንጸባርቃል።
- የሚናገራቸውን ሳዳምጥ ተስፋ የሚሰጡ ናቸው። ስለዚህ፤ አብይ በኢህአዴግ "ታነጸ" ቢባልም በመለወጥ ላይ መሆኑ ይታያል። አንድ ግለሰብ አይለወጥም የሚል ብሂል ድንቁርና ነው። ለማሰብ የሚችል ግለሰብ ይለወጣል።
- ስለዚህ፤ በምንም አይለወጥም ከሚለው ይልቅ **<u>ሊለወጥ ይችላል</u>** የሚለውን ማስቀደምን እመርጣለሁ።

ይህ እንዳለ ሆኖ፤ ዶር አብይ የቆመው ለመሰረታዊ ለውጦች ነው ወይንስ ለተመለደው የህወሓት/ኢህአዴግ ጥገናዊ ለውጦች ነው? የሚለው መሰረታዊ ጥያቄ ገና አልተመለሰም። ይህ ወጣት መሪ መሪ እንዲሆን የተደረገው በኢህአዴግ አመራር ብልጫ ያለውን ድምጽ አግኝቶ ነው። ከዚህ ጀርባ ግን ለውድድር እንዲቀርብ የህወሓት ድጋፍ አለበት ወይስ የለበትም? የሚለው ጥያቄ ገና አልተመለሰም። ዶር ደብረጽዮን ሁለት ድምጽ ብቻ አገኘ የሚለውም ከጀርባ ያለውን ስትራተጂ ይስታል፤ አናውቀውም። የህወሓትን መሰሪነት በጥንቃቄ ማየት አለብን፤ ቶሎ አንፍረድ። በእኔ ግምገማ፤ ህወሓት **ይኑርበት አይኑርበት አብይ ተወዳድሮ ተመርጧል። ወደፊት ከምን ላይ ያተኩራል የሚለው በሂደት የሚታይ ነው። <u>ያም ሆኖ፤ ወታደሩ፤ ጸጥታው፤ ኢኮኖሚውና "ፓርላማው" በህወሓት ሙሉ ቁጥጥር ስር እስከሆኑ ድረስ፤ የስርዓት ለውጥ ይመጣል ብየ ራሴን አላታልልም።</u>**

ዶር አብይ ከኦሮሞ ኢትዮጵያዊያን መካከል "የመጀመሪያው የኢትዮጵያ መሪ ነው" የሚለው ትክክል አይደለም። የቅርቡን ብቻ ምሳሌ ብጠቀስ፤ **<u>አቶ ተስፋየ ዲንቃ</u>** የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚንስትር ነበር።

የዶር አብይ መመረጥ መታየት ያለበት ከሚከተሉት አስኳል ብሄራዊ ጉዳዮች አንጻር ነው የሚል እምነት አለኝ።

አንደኛ፤ ሕዝቡ የሚፈልገውን መሰረታዊ ለውጥ ለማመቻቸትና ለመግፋት ይችላል ወይስ የህወሓትን/የኢህአዴግን መስመር ይዞ ይቀጥላል? የህወሓት/ኢህአዴግን መስመር ይዞ ከቀጠለ ለጊዜው ሕዝባዊ አመጹ ጋብ ሊል ይችላል። ዘላቂ ሰላም፤ እርጋታ፤ ፍትሃዊና ተከታታይ እድገት አይኖርም። ፍትህ የሚባል ነገር አይታሰብም። ይኼን የሚያጠናክረው ህወሓት/ኢህአዴግ ያወጣው መግለጫና ጥሪ ነው። የተረጋጋ ሰላም በአገሪቱ ሊኖር የሚችል አይመስለኝም።

ቁም ነገሩ፤ ዶር አብይ የሕዝቡን፤ በተለይ የወጣቱን ስሜት ከቀሰቀሰ በኋላ ወደፊት ባለው ሚናው ይህን ሰፊ ሕዝብ ያገለግል ይሆን? የሚለው ጥያቄ በሂደት ይታያል።

ስለዚህ፤ የሕዝቡ መሰረታዊ የፍትህ ጥያቄዎች ካልተመለሱ፤ ሕዝቡ እንደገና በባሰ ሁኔታ ይነሳል የሚል እምነት አለኝ።

ሁለተኛ፤ የዶር አብይ መመረጥ በተናጠል የሚታይ አይደለም። ከኦሮሞው ሕዝብ፤ በተለይ ከቄሮው የትግል ውጤት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው። አብይ ለኦሮሞው ሕዝብ በተለይ ለወጣቱ ትውልድ (ለቄሮው) ሃላፊነትና ውለታ አለበት። ተጠያቂም መሆኑ

አይቀርም። ከዚህ ባሻገር፤ አዲስ ደፋርና ቅንነት ያለው መሪ ተመርጧል ለማለት የምደፍረው አብይ የሁሉንም ኢትዮጵያዊያን የፍትህ ፍላጎት ለማሟላት ሲሞክር ነው። በእኔ ግምት፤ ይሞክራል።

ሶስተኛ፤ በእኔ እምነት የዶር አብይ መመረጥ፤ ለኦሮሞው ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጭምር ነው። ይኼን የሚያመለክተው ከብአዴን አመራር አባላት ከፍተኛውን ድምጽ ማግኘቱ ነው። ደመቀ መኮነን ራሱን ከውድድሩ ማግለሉ አግባብ አለው። በምንም መስፈርት ደመቀ ለጠቅላይ ሚንስትርነት ብቃት የለውም። ከአብይ ጋር ሊነጻጸር አይችልም። ሌሎቹም ተወዳዳሪዎች የራሳቸው ድክመቶች አሏቸው። ሌላው አብይ **ኢትዮጵያዊነትን ማጠናከርና ኢትዮጵያን** ከአደጋ መታደግ ወሳኝ መሆኑን በተደጋጋሚ ማሳሰቡ ነው። ይህ አርቆ አስተዋይነቱን ያሳያል። ይህን ስኬታማ ለማድረግ ከቻለ ታሪክ ሰሪ ይሆናል።

አራተኛ፤ ህወሓት/ኢህአዴግ ኢትዮጵያን ለመምራት የሞራል፤ የአመራር፤ የድርጅት ብቃት የለውም። አባላት አሉኝ ቢልም፤ ውስጡ ቀፎ ነው። ከጊዜው ጋር የሚሄድ ድርጅት አይደለም። የአብይ መመረጥ ስርዓቱ የፈጠራቸውን ተግዳሮቶች (Systemic hurdles) አይፈታቸውም። ነገሮችን በማብረድና መሰረታዊ ለውጦችን ስኬታማ በማድረግ መካከል የሰማይና የምድር ልዩነት አለ። አብይ ጥገናዊ ለውጦችን ስኬታማ ለማድረግ ይችል ይሆናል። ይኼም በሂደት ይታያል።

አምስተኛ፤ ኢትዮጵያ የብሄራዊ መከላከያ፤ የብሄራዊ ደህንነት፤ የብሄራዊ የፍርድ አስተዳደር፤ የብሄራዊ የውጭ ግንኙነትና ሌሎች አስፈላጊ ብሄራዊ ተቋሞች የሏትም። በተለይ የመከላከያውና የደህንነት ተቋሞቹ በህወሓት የበላይነት መያዛቸው ለአገሪቷን ለሕዝቧ አደገኛ ሆኔታዎችን ፈጥረዋል። የእነዚህ ተቋሞች ዋና ሚና አገርን ከውጭ ጠላቶች ለመከላከል ነው። ሕዝብን ለማፈን፤ ለመጨፍጨፍ አይደለም። እነዚህ **ተቋሞች ከህወሓት ቁጥጥር ነጻ ሆነው ብሄራዊ ካልሆኑ** ለአዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር ችግሮችን እንደሚፈጥር እገምታለሁ። **አንዱ በአስቸኳይ መፈታት ያለበት ይኼው ተግዳሮት ነው።**

ስድስተኛ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይ ወጣቱ ትውልድ ዶር አብይ ስለተመረጠ ብቻ ሕዝባዊ ዐመጹን ማቆም የለበትም። እንዲያውም፤ ይህ ወጣት መሪ በተቻለው መጠን **ለመሰረታዊ ለውጥ ድልድይ** እንዲሆን ከተፈለገ ሕዝቡ እምቢተኛነቱን መቀጠል አለበት።

ሰባተኛ፤ በመሰረታዊ ለውጥ መስፈርት ከገመገምነው፤ አብይ ብዙ ፈተናዎች ይገጥሙታል። ከላይ እንዳቀርብኩት፤ም ከእነዚህ መካከል የመከለካያና የደህነነት ተቋሞቹ አሁንም በህወሓት ስር መሆናቸው ነው። ይህ **"ሁለት መንግሥት በአንድ አገር"** ከቀጠለ ሁኔታውን ያባብሰዋል። እነዚህ ተቋሞች ከማንም ፖለቲካ ፓርቲ ቁጥጥር ውጭ ሆነው፤ በጠቅላይ ሚንስትሩ ስር እንዲሆኑ ግፊት መደረግ አለበት። አለያ፤ "ሁለት መንግሥታት" ይቀጥላሉ። አንዱ የህወሓት፤ ሌላው በኦህዴድ የሚመራው የኢህአዴግ መንግሥት። እኔን የሚያሳስበኝ "ሁለት መንግሥታት" የሚለው ከቀጠለ፤ ኢትዮጵያ ከውጭ በሚመጣ ኃይል ልትጠቃ ትችላለች። አብይ ይኼን ወጥመድ (hook) እንዴት እንደሚፈታው ወደፊት ይታያል።

ስምንተኛ፤ በኢህአዴግ ውስጥ **በለውጥ ፈላጊዎችና ባለው እንርጋ ባዮች (Status quo) መካከል** የተከሰተው ልዩነት ገና የተፈታ አይመስለኝም። አብይ ይህን ልዩነት ለመሰረታዊ ለውጥ ጫና ቢጠቀምበት የተሻለ ውጤት ይኖራል። አባል ድርጅቶች፤ በተለይ **ብአዴንና ኦህዴድ ራሳቸውን ከህወሓት ሎሌነት ነጻ** ማድረግ አለባቸው። የመጀመሪያው ስራቸው ራሳቸውን ከህወሓት ሰርጎ ገቦች ነጻ ማውጣት ነው። በእነዚህ ድርጅቶች ውስጥ ጠንካራ ኢትዮጵያዊያን እንዳሉ አምናለሁ። እነዚህ አባላት፤ ከመቸውም በበለጠ ደረጃ ትግል አካሂደዋል። ልዩነቶቻቸውን በድፍረት የገለጹበት ዋና ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ ስላሰገደዳቸው ነው። ሌላው ምክንያት፤ ኢትዮጵያ **አደገኛ ወደሆነ ቀውስ** ውስጥ ሰለገባችና ገዢው ፓርቲ ለቀውሱ ብቃት ያለው አመራር ለመስጠት ስላልቻለ ነው። በዚህ መስፈርት ሲታይ፤ ህወሓት/ኢህአዴግ ተሸንፏል። እየዋሸና ሕዝብን እየሸነገለ ሊገዛ አይችልም። ይኼን ክፍተትና ድክመት አብይ ሊጠቀምበት ይገባል። **ሆኖም፤ የሕዝብ ድጋፍ ያስፈልገዋል።**

ዶር አብይ የሕዝብን፤ በተለይ የወጣቱን ትውልድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ብቻ ሳይሆን፤ ለፍትህና ለሕግ የበላይነት መቆሙን በማያሻማ ደረጃ ለማሳየት ያቀረባቸው ትንተናዎችና ዘገባዎች ትምህርታዊ ግብአቶች ናቸው። ከሳቡኝ አበይት ብሄራዊ ቁም ነገሮች መካከል፤

- "የብሄር፤ ብሄረሰብና ሕዝቦች እኩልነት"፤ ፍትሃዊነት፤ የዲሞክራሲ ምህዳር መስፋፋት፤ የማንነት ስኬታማነትና ተቀባይነት ለኢትዮጵያዊነትንና ለኢትዮጵያ መጠናከር ወሳኝ መሆናቸውን ማስመሩ ነው። ኢትዮጵያ ከሌለች እነዚህ ሁሉ የውሃ ሺታ እንደሚሆኑም ተናግሯል።
- ከህወሓቶች በተለየ ሁኔታና አንደበት **"ሥልጣን እንደ እርስት" የሚወረስ፤** የሚሰጥና የሚነሳ አይደለም" ያለው ከህወሓት መሪዎች መርህ ይለያል። ከዚህ ጋር አያይዞ፤ እኔ ብዙ ጊዜ ያሳሰብኩትን "የፖለቲካ ሥልጣን ዋናው የኃብትና የጥሪት መሰብሰቢያ መሳሪያ መሆኑን" ለኢህአዴግ አመራር አቅርቦታል። ይህ ባህል መወገድ አለበት።
- የዲሞክራሲ ስርዓት ለቅንጦት አይደለም። አብይ "የዲሞክራሲ መስፋፋት የህልውና ጉዳይ ነው" ያለው ትክክል ነው። በተመሳሳይ፤ የሰብአዊ መብቶች መከበር ከፍትህ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው መሆኑን አስምሮበታል። "ፍትህ ከዳቦ ያላነሰ" የሙብት ጥያቄ ነው ብሏል። **ይህ ብቻ አይደለም፤ የህልውና ጥያቄም ጭምር ነው።**
- ህወሓት/ኢህአዴግ የሚታወቀው በኪራይ ሰብሳቢነት፤ በሙስና፤ በጎሳዊ አድልዎ ነው። የኃብት ክፍፍልንና ክምችትን ሁኔታው አባብሶታል። ይህ ለቀውስና ለግጭቶች መበባባስ መንስኤ ሆኗል። ገበያውን አዳከሞታል። ኮንትሮባንዱን

አስፋፍቶታል። ከቁንጮው ያሉት ሙሰኞች ለሕግ እንዳይቀርቡ ህወሓት ተገን ሆኗቸዋል። እነዚህ ሁሉ ለአብሮነት ማነቆ መሆናቸውን አብይ ጠቁሟል።

አከራካሪ የሆነው የአብይ ዘገባ የፌደራል አስተዳደሩን ይመለከታል። ይህን ጉዳይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተመካክሮ ወደፊት ሊወስነው ይገባል። አብይና አንዳንድ ምሁራን የሚሉት ችግሩ የፌደራል ስርዓቱ ሳይሆን አፈጻጸሙ ነው። የእኔ ዘገባ ከዚህ የተለየ ነው። ሕገ መንግሥቱ የኢትዮጵያን ዜጎች መአከል ያላደረገ ነው። በፌደራሉ መንግሥትና በክልሎች መካከል ሊኖር የሚገባውን አስተዳደር በጥናትና በምርምር ተደግፎ አልተዋቀረም። ምን አይነት ፌደራሊዝም የሚለው የጥቂት ብሄርተኞች ውሳኔ እንጅ የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ውሳኔ አይደለም። ይህ ልዩነት እንዳለ ሆኖ፤ ዶር አብይ ያቀረባቸው አግባብ አላቸው። በሁሉም አበይት ጉዳዮች ላይ መስማማት አያስፈልግም። ላለመስማማት መስማማት ይኖርብናል። አስቀድመን አንተቸው።

**አብይ ምን ለማድረግ ይችላል?**

1. በቀርቡና በፊት የታሰሩትን የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ በአስቸኳይ መፍታት አለበት። የዋልድባ መነኮሳትና አባቶች ሳይውል ሳያድር መፈታት አለባቸው።

**የሕዝብ ጥያቄዎች ይመለሱ**

2. ዶር አብይ መልካምና ብቃት ያለው መሪ ሊሆን ቢችልም፤ ከአሁን በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙ መስዋእት ከፍሎ መሰረታዊዎቹ ችግሮች ካልተፈቱለት ማንንም አይቀበልም።

3. ህወሓት/ኢህአዴግ "ራሴን ገምግሜአለሁ፤ ሕዝብን ይቅርታ ጠይቄአለሁ" ቢልም ርእዩቱ፣ ተልእኮውና ፕሮግራሙ ካልተለወጡና ሕዝቡ የፖለቲካ ሥልጣኑ ባለቤት፤ የተፈጥሮና የሌላው ኃብቱ ባለቤት እስካልሆነ ድረስ፤ ነጻነቱና ሰብአዊ መብቶቹ እስካልተከበሩ ድረስ "በባርነት የሚገዛውን" አምባገነኑን ስርዓት ተቀብሎ አይኖርም። <u>**መሰረታዊ ለውጥ ለኢትዮጵያ ሕልውናና ለሕዝቧ ደህንነት ወሳኝ ነው። የሕዝቡም መሰረታዊ ጥያቄዎች ናቸው።**</u>

4. ህወሓት ምንም አይነት መሰረታዊ ለውጥ ለመቀበል ፈቃደኛ እንዳልሆነ በመቀሌ የጠራው ሰላማዊ ሰልፍ ያሳያል። በመቀሌ ከተማ የተካሄደው የአብይን ተቃውሞ የማየው እንደ ፖለቲካው ውሳኔ ነው። የትግራይ ሕዝብ ውሳኔ አይመስለኝም። እኔ እስከማውቀው ድረስ ዶር አብይ ከማንኛውም 'የፖለቲካ መሪዎች ነን' ባዮች መካከል በጸባዩ፤ በሞራል ብቃቱ፤ በትህትናው፤ በአስተዋይነቱ፤ በሰፊ እውቀቱ፤ በሞያዎቹ፤ በአርቆ አስተዋይነቱ፤ ነገሮችን ሚዛናዊ በሆነ ደረጃ ለመተንተንና ወደ አስፈላጊው ድምዳሜ ለመድረስ ባሳያቸው የመሪነት ብቃቱ ወዘተርፈ ተወዳዳሪ የለውም።

5. እኔን የገረመኝ ይኼን እያወቁ ህወሓቶች ዶር ደብረጽዮንን ለምን ተወዳዳሪ እንዳደረጉት ነው። ወይንስ የህወሕት ድብቅ ስልት ነው?

6. ዶር አብይ የኦሮሞው ዘውግ አባል ስለሆነ አይደለም የተመረጠው፤ ብቃትና ጥራት ያለው ተስፋ የሚሰጥ መሪ በመሆኑ ነው ከመቶ በላይ ድምጽ ያገኘው።

7. ይህን ስል፤ ዶር አብይም ሆነ ሌላ መሪ የኢትዮጵያን ግዙፍ ችግሮች ይወጣቸዋል ማለቴ አይደለም። ማንም ሊቀርፋቸው የማይቻሉ የፖሊሲ፤ የመዋቅርና ሌሎች ችግሮች አሉ። እነዚህን ስርዓታዊ ተግዳሮቶች (Systemic hurdles) ለመወጣት የሚቻለው በሕዝብ ተሳትፎ፤ የአጭርንና የረዢም ጊዜ የስራ እቅዶችን በመቀየስ፤ ኢትዮጵያዊ ተቋሞችንና ሰራተኞችን እንደገና አቋቁሞ የሰራተኛውን፤ በተለይ የወጣቱን ትውልድ ክፍል አቅም በማጎልመስ፤ ሙስናንና አድልዎን በማስወገድ፤ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ በማካሄድ፤ የእርቅ፤ የሰላም፤ የብሄራዊ መግባባትና የሽግግር ጉባኤ እንዲካሄድ በማመቻቸት ወዘተ ነው።
8. በመጨረሻ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚመኘው ሁሉን የሚያሳትፍ የእርቅ፤ የሰላም፤ የብሄራዊ መግባባትና ሁሉን አሳታፊ የሆነ የሽግግር መንግሥት እንዲመሰረት ነው። ዶር አብይ ይኼን ለማድረግ ይችል ይሆን?

**ተከታታዮቹ ወደፊት ይሰራጫሉ**

*መረጃ*

**https://www.aljazeera.com/indepth/opinion/tough-road-ethiopia-leader-abiy-ahmed-180331070649693.html**

April 1, 2018